# ጥቁር ነው አባማ?

ከትንሣኤ - tinsaelehager@ymail.com - ጥቅምት 2001



በምን አገላለጽ በምን ትርጓሜ፣
በምንስ ትንተና በማንስ ስያሜ፤
ጥቁር የተባለው አባማ ወንድሜ?
ይሆን የጥቁር ደም "ዶሚናንት" ተብሎ፣
ከነጩ የገነነ እኩል ተቀላቅሎ?
ወይስ የነጭ ኩራት ትምክህት አይሎ፣
የጥቁር "ጂን" ንቆ፣ ጥሎና አጣጥሎ?
የማይሆን ትርጉም ነው እንዲያው የተለምዶ፣
ክብር ከየት ይመጣል ራስን አዋርዶ።
በእናቱ ነጭ ሆኖ በአባቱ ሲጠቁር፣
መሳ ለመሳ ነው "የክሮሞዞሙ" ቁጥር።
አንም ጠቁራ ይሆን ከጥቁር ብትተኛ፣
ነጮች አግልለዋት ብለው ሞገደኛ?
ሁሉም ሰው ሲገባው የጠፋብኝ መላ፣
ያስተማሩኝ ሣይንስ ቢነግረኝ ነው ሌላ።
የተኛበት ማኅጸን የተንተራሰበት፣
የነጭም አልነበር የቆረጡት እትብት?
እኔ እንደሚገባኝ ...
የ"ናይሎቲክ" ግንዱን የቸረው አባቱ፣
ጥቁር መሆኑን ነው ስረ መሰረቱ።
ነጭ ነች እናቱ ይህ የታወቀ ነው፣
ማን በተረጎመው ጥቁር እምንለው?
ስለአሉን ነው እምንል ገብቶን ነው ነገሩ፣
የዘር ሀረግ ፍቺው ቀለም አጠራሩ?
የዘር አመጣጡ ውልደቱ ሲወሳ፣
ቅይጥም አይደለ የሆነ አምሳ ባምሳ?
አባማ ውህደት ነው ራዕይ የአሜሪካ፣
የነጭ የጥቁር ዘር ቅይጥ ነው "ወልመካ"።
ራዕይ የተሞላ ባለ ቀለም አልባ፣
የነጭ የጥቁር ዘር ፍሬ ነው አበባ።
ነጭ ጥቁር ሳይል እጅ ለእጅ አስይዞ፣
ተስፋን አስጨብጦ የጀመረ ጉዞ፤
በአንድ አይገደብም ሁሉን ነው አባማ፣
ከቀለም በላይ ነው የያዘው ዓላማ።
በጾታውም ቢሆን ...
ወንድ ብቻ አይደለም ሴት ነው በግማሹ፣
ጭንቀት የሚገባው የትልቅ ትንሹ።

ችግርና ኀዘን የአያትና እናቱ፣
ፍቅርና ኅብር ልጆቹና ሚስቱ፤
በሴት ብልህነት ለዚህ የመብቃቱ።
ሁሉን ያካተተ ለለውጥ የተነሳ፣
ትጉኅ ነው እንበለው ጾታውን አናንሳ።
**በጥቁር ላይ ነጭ ነው** በነጭ ላይ ጥቁር፣
ፍሊጋው ከንቱ ነው ለአንዱ ለመመስከር።
አሜሪካ የታየች በዓለም ላይ ጎልብታ፣
ነጭ ጥቁር ሳትል ብትተጋ ነው ሠርታ።
የነጭ የጥቁር ደም ቅልቅል "ወልመካ"፣
አባማ ውህደት ነው ራዕይ የአሜሪካ።
የኔንም ሳስበው ...
እንዲህ ነህ ተብዬ በግድ እምጠራ፣
እንዴት ነው ኦሮሞ እንዴትስ አማራ?
ኢትዮጵያዬ ሳለች ክብሬና ማዕረጌ።
እንዴትስ ነው ትግሬ ለምንስ ጉራጌ?
ሁሉ አለኝ በደሜ እማልዘልቀው ቆጥሬ፣
ነጻነት ፍትህ ነው እጦቴ ችግሬ።
የሁሉም ነፃነት ካልሆነ ዓላማዬ፣
ኑሮዬ እልፍ አይል በዘር ቆጠራዬ።
ዙርያውን የማየው አጉል ነው ሽንገላ፣
አናክሶ የመጣል መሰሪ "ፎርሙላ"።
አበላልጠው ኖረው ሁቱውን ከቱትሲ፣
ሲጫረስ ሳቁበት በስመ ዲሞክራሲ።
አብረው እንዳልኖሩ ጆርጅያና ራሽያ፣
ለታንክ ለባዙቃ ሆኑ መሞከሪያ።
ተማምለው ከፍለው ኤርትራን ከኢትዮጵያ፣
መቼ ፍቅር መጣ መች ቆመስ ግድያ?
ይህ አጉል መጃጃል ቁልቁል ዘር ቆጠራ፣
ተባልቶ ማለቅ ነው በተራ በተራ።
እኛ ስንጫረስ ተናክሰን እርስ በእርስ፣
ይቀራመቷታል ኢትዮጵያን ቀስ በቀስ።
እኔም ኢትዮጵያዊው የሰው ልጅ ዘር ግንዱ፣
እሺ ብዬ አላይም በእኔው ሲነግዱ።
በኢትዮጵያዊነቴ አጥብቄ እምመካ፣
የብዙ ዘር ኅብር ቅይጥ ነኝ "ወልመካ"።

*የአመለካከት አቅጣጫን ሊያስቀይር የቀለም ልዩነትን ሊያደበዝዝና እጅግ አደገኛና አስቸጋሪ በሆነ ታሪካዊ ወቅት ተስፋን ለመዝራት ለሚተጋው የሁለት ቀለም ውሁድ ለአባማ አሸናፊነትን እመኛለሁ። የሰው ልጅ ዘር ግንድ በመሆናቸው የሚኮሩ ኢትዮጵያውያን ከጎጥና ከመንደር እንዲሁም ከግል ክብርና ዝና በላይ የሆነ ራዕይ ይኖራቸው ዘንድ እማጸናለሁ።*

**ከትንሣኤ - tinsaelehager@ymail.com - ጥቅምት 2001**

http://EthiopiaZare.com